
# ከልደት እስከሞት

ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቅን ፲፱፻፷፩ ዓመት ምህረት



**ከደጃዝማች ኪዳኔ ወልደ መድኅን**
**የተደረሰ አጭር መጽሐፍ**

ሰይፈ ገብርኤል ኪዳኔ
ለንደን
መጋቢት ፲ ቀን ፲፱፻፺፺ ዓመተ ምህረት

# <u>መቅድም</u>

ከልደት እስከ ሞት የተባለበት ምክንያቱ ሰው በእግዚአብሄር ፈቃድ ከመሬት፣ ከውሃ፣ ከእሳት እና  ከነፋስ ተፈጥሮ በላብህ ወዝ ጥረህ ግረህ ብላ ተብሎ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት የሰው ልጅ ከአባቱ አብራክ ወደ እናቱ ማህጸን ተላልፎ አጥንትና ስጋ ከነፍስ ጋር ተዋህዶ ፱ ወር ከ ፭ ቀን በእናቱ ማህጸን ቆይቶ ለጣር አጋር ወደዚህ ዓለም ይመጣል ።  ከመጣም በኋላ ፫ ዓመት በእናቱ እጅ አባባ እማማ እያለ ቆይቶ ፬ ዓመት ሲሆነው ለትምህርት ፤ ለእረኝነት ወይም በሌላ ልዩ ልዩ ተግባሮች ተሰማርቶ አሥራ አምስት ወይም አሥራ ስምንት ዓመት እስኪሞላው ድረስ በወላጆቹ ወይም በቤተሰቦቹ ስር በሚቆይበት ጊዜ በዚህ ዓለም ለሰው ልጅ መተዳደሪያ የሚሆኑትን ማናቸውንም የኑሮ አቓም ሁሉ ባካባቢውና በሰው እጅ ሲመለከተው እንደ ሰሜን ተራራ ርቆት ስለሚያየው፤ እኔም እንደዚህ እንደማያቸው ሰዎች ራሴን ችዬ በህይወተ ሥጋ ያለውን አቓሜን ለማስተዳደር በሰብአዊነቴ ችግረኞችንና በሽተኞችን ለመርዳት ህገ እግዚአብሔርንና ሕገ መንግስትን ጠብቄ ለመኖር አብቃኝ እያለ እግዚአብሄርን በመለመን በህሊናው ሲያወጣና ሲያወርድ ሲመኝ ይቆያል።

እግዚአብሄርም የለመኑትን የማይነሳ የነገሩትን የማይረሳ ነውና በአርባ ቀን የሰጠውን እድሉን አቃንቶ፤

(ሀ) በቤተ መንግስት - በወታደርነት፤ በጸኃፊነት፤ በአስተዳደር ሌላም በልዩ ልዩ ሥራዎች፤

(ለ) በቤት ክህነት-  በቅስና፤ በድቁና፤ በድብትርና

(ሐ) በንግድ - ሸቀጥ አስመጪና ላኪ፤ ደላላ፤ የሱቅ ነጋዴ በመሆን

(መ) በግብርና - እርሻና ከብት እርባታ

(ሠ) በጠቅላላ አስተዳደር - ጳጳስ፤ ንጉስ በመሆን

በየገጹ ተሰማርቶ የስጋውንና የነፍሱን አቓም በመጣር በመጋር ለስራ ታጥቆ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ በመዋእለ ዘመኑ የሚያጋጥሙትን መከራና ስቃይ

ተቓቁሞ ለህሊናው እረፍት ሳይሰጠው እና ይህን ዓለም ሳይጠግበው እንዳልነበረ ሆኖ ቀሪ መሆኑን ለማስታወስ ያህል ነው።

ይህችን መጽሐፍ በአነስተኛ ቃላት ለአንባቢዎች ሳበረክት ምናልባት በቃላቱ አሰካክና በፊደላቱ አቀማመጥ ስህተት ቢኖር በትህትና አርሙኝ እያልኩ በተጨማሪም ድርሰቱ ህገ ወጥ የሆኑትን ስለሚጠቅስ ሕግ የምታስተው ሥጋ ነገ በስባሽ ፈራሽ ሆና ከመሬት የምትቀር ሲሆን፤ ነፍስ ግን በቅድመ እግዚአብሔር ዘንድ ወቀሳና ፍርድ ያለባት መሆንዋን አስበው ነቀፌታን ከመሰንዘር ሐሳቤን እንዲደግፉኝ እለምናልሁ።

## ማሕጸነ ዓለም

የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ትእዛዝ "ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ኦሪት ዘፍጥረት ምእራፍ ፩ ቁጥር ፳፮ ባለው መሰረት ከአራቱ ባሕርያት፤- ከነፋስ፤ ከውሃ፤ ከእሳትና ከመሬት በደማዊት፤ በልባዊት፤ በቃላዊት ነፍስ ተዋሕዶ መፈጠሩ በሊቃውንቶች ይነገራል።

በዚህ መሰረት ተፈጥሮ በእናቱ ማህጸን ከተዋሃደ በኋላ ፵ ከ ፹ ቀን ቆይቶ ወደ እዚህ ዓለም ሊጥር ሊግር ለዓዳምም በተነገረው መሠረት በላቡ ወዝ እንዲበላ ወደ ልደተ ዓለም ይመጣል።

## ልደተ ዓለም

የሰው ልጅ ወደ ልደተ ዓለም ከመጣ በኋላ ፫ ዓመት እስከሚሞላው ከእሳት፤ ከገደልና ከልዩ ልዩ አደጋዎች በእናቱ ኃላፊነት ተጠብቆ ቆይቶ ፬ ዓመት ሲሞላው አንዱ ወደ ትምህርት፤- በቤት ክህነት ወይም በዘማናዊ ትምህርት፤ የገጠሩ ወገን ደግሞ ወደ እረኛነት ቆየት ሲልም ወደ ግብርና፤ ሌላው ወገን ወደ ንግድ በልዩ ልዩ መስመር ተሰማርተው ፲፮ ወይም ፲፰ ዓመት እስከሚሞላቸው በሥጋዊ ዓለምና በመንፈሳዊ ዓለም መሪነት ተግባራቸውን ይቀጥላሉ።

በዚህ ጊዜ አቶ የሥጋ ምኞት የተባለው ሽማግሌ ወደ ሥጋዊ ዓለም መኖርያ ቤት መጥቶ "አቶ ሥጋዊ ዓለም፤ ኑሮህን ለማስፋፋትና በዚህ ዓለም ለመከበር፣ ለመታውቅ፣ ለመበልጸግ ብትፈልግ የቅርብ ረዳትህ

የሚሆኑ ባልደረቦቼን (ሀ) ንፍገትን (ለ) ቅናትን (ሐ) ተንኮልን (መ) ምቀኝነትን (ሠ) ኩራትን (ረ) ስስትን (ሰ) ሴሰኝነትን (ሸ) ቁጡነትን እነዚህን ስምንት የቀድሞ ሰዎች፤ ፀ፻ እኔን የሥጋ ምኞትን ይዘህ ቤትህንና ንብረትህን በመደጋገፍ ካላስከበርከው በገንዘብህና በእውቀትህ ከሰው በላይ ሆነህ ካልታየህና ካልተፈራህ፤ አዋቂ፣ ጀግና፣ ሃብታም እና ባለጸጋ የሚባል ቅጽል ስም ልታገኝ አትችልም። ስለዚህ እነዚህን በስም የተጠቀሱ ሰዎች ወደቤትህ አስጠራና አብረዉህ እንዲኖሩ አነጋግራቸው። ለኑሮህ መብራትና ፋና በመሆን ሞገስ ታገኝ ዘንድ የልብ ምክሬን አበርክቶልሃለሁ።" ሲለው አቶ ሥጋዊ ዓለም በነገሩ ተደስቶበት እና አምኖበት፤ በቶሎ ይጠሩልኝ ብሎ ይልከዋል።

አቶ መንፈሳዊ ምኞት ይሄንን ውይይት በስተቀኝ ቆሞ ይሰማ ነበርና፤ "አቶ የሥጋ ምኞት ሳይመጣ አንድ ነገር ላስታውስህ። አቶ የሥጋ ዓለም፤ አሁን አቶ የሥጋ ምኞት የሚልህ በስም የዘረዘራቸውን ሰዎች ባጠገብህ አድርገህ ለኑሮህ ደጋፊና መካሪ እንዲሆኑ ሲል በሰጠህ ምክር ተስማምተህበታል፡ በእኔ በኩል የምመክርህ ግን በዚህም ሆነ በዚያኛው ዓለም የሚጠቅምህ እግዚአብሄር የሰውን ልጅ በላቡ ወዝ ጥሮ ግሮ እንዲበላ ሲያዘው በኑሮ ዘመኑ ሁሉ ምቀኝነትን፤ ተንኮልን፤ ንፍገትን፤ ኩራትንና የሰውን ገንዘብ መመኘትን፤ ስስትን እንዳይከተል ፤ሕገ ኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ ፳፫ ቁጥር ፲፯ እስከ ፩፱ ቸርነትንና ርህራሄን፤ ደግነትን፤ ተካፍሎ መብላትን፤እምነትን እንዲከተል የሰጠው ትዕዛዝ መሆኑን ተመልከት። የአቶ ሥጋ ምኞትንም ምክር መከተል በሰማያዊው ንጉስ ዘንድ በግራ ቆሞ የዘለዓለም ፍዳ ያስፈርዳል፤ የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፭ ቁጥር ፴፩ እስከ ፵፮።"

አት ሥጋ ዓለም ይሄን ሰምቶ፤ "አዬ እባክህ ይህንን የምትለውን በመጽሐፍ ቢጻፍ እሰማይ ማን ወጥቶ አየ? እኔስ በዚህ ዓለም ላይ ተድላን ደስታን በማግኘት በሰው ዘንድ መፈራትን፡ መከበርን አግኝቼ ይቅርብኝ።" ይለዋል መንፈሳዊ ምኞትም "አየህ የሥጋ ዓለም፤ አንተማ ምን ታደርግ በዚህ ዓለም ሥጋህን አለምልመህ አንተ በጫርከው እሳትና ባመጣኸው መከራ አቶ ጻዕረ ሞት ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን አፍጥጦ ሲመጣ እንደንብ ቀፎና እንደ እባብ ግልፋፊ ውልቅ ብለህ ቀርተህ በተማሰልህ ጉድጓድ ገብተህ ለጥ ትላታለህ፡ እኔ እንጂ ባለመከራው በዚህ ዓለም ስኖር አንተ በምትሠራው ግፍና መከራ ስባንንና ስሰጋ፡ ተው ብልህ አትሰማ፡ በኃላም የሞት ጥሪ ደብዳቤ ሲመጣ አንተ ከድትኸኝ ትቀራለህ፡ እነ አጅሬ የጥልምያኮስ ጭፍሮች እያክለፈለፉ ከጭራ በቀጠነች መንገድ ግራና ቀኝ የእሳት ገደልና ውሃን፡ እሳት

እንደገባች ጅማት እየተኮማተርኩ ከመቅጽበት ከፊጣሪያችን ፊት ቀርቤ ጥያቄ ሲቀርብልኝ ምን ልመልስ ነው? አንተ ከዚህ ቀሪ።

እስኪ ቢሆንም እኔና አንተ ብቻ ከምንከራከር አቶ አስተዋይ ልቦናን፤ አቶ ቸርነትን፤ አቶ ደግነትን፤ አቶ ርህራሄን፤ አቶ ብልህን ጨምረን እንወያይበት፤ ብሎ ሲያስረዳው፡ አቶ ሥጋ ዓለም በነገሩ አልስማማም፤ እኔ የምትላቸውን ሰዎች እንክዋን ምክር ላካፍላቸው ቀርቶ በዓይኔም ማየት አልፈቅድምና ይቅርታ አድርግልኝ። የግብረ አበሮቹ እነ አቶ ተንኮል መምጫቸው ደርሶአልና ልቀቅልኝ ብሎት መንፈሳዊ ምኞት በነገሩ ተጸጽቶ ሲወጣ፡ በስም የተጠቀሱትና መልክተኛ የተላከባቸው አቶ የሥጋ ምኞትን አስቀድመው ከተፍ ብለው ለአቶ ሥጋዊ ዓለም ሰላምታ ያቀርባሉ። ወዲያውም ሥጋ ምኞት በየሥራቸው ለአቶ ሥጋ ዓለም ያስተዋውቃቸዋል። ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን ነገሮች የግብረ አበሮቹ በመሆን በክብር ክብር፤ በደስታ ላይ ደስታ እንዳይለየው እንዲያደርጉለት ያናግራቸዋል።

አቶ የሥጋ ምኞት ከመቀመጫው ብድግ ብሎ "አቶ ሥጋዊ ዓለም አይዞህ፤ እኔ የምኞት ጌታ አቶ ቅንአትን፤ አቶ ተንኮልን፤ አቶ ምቀኝነትን፤ አቶ ትዕቢትን፤ አቶ ንፍገትን፤ አቶ ኩራትን፤ አቶ ክፋትን ይዤ አንተን ከሰው በላይ ሳላደርግህና እንድትከበርና እንድትፈራ ሳላደርግ ብቀር፤ በምጽአት ጊዜ ዲያብሎስ አላውቅህም ይበለኝ፡ አታስብ ግዴለህም ታላላቅና ሀብታም ሆነው ለምታያቸው ሰዎች አቶ ተንኮልንና አቶ ምቀኝነትን ሴሰኝነትን አቶ ንፍገት እኮ ናቸው።

የሰው በላይ በመሆን በሰማይ መብረርን፤ በምድር መሽከርከርን፤ በሰማይ ጠቀስ ሕንጻ መንፈላሰስ በጠቅላላው ድሎት የሚባለው የሚገኘው በነዚህ ጠንካሮች ሰዎች ዕርዳታ እንጂ እነ አቶ ቸርነት፤ እነ አቶ ደግነት፤ እነ አቶ አብረን እንብላ እንጠጣ ዛሬ በአል ነው አንሰራም በማለት የስንፍና ጭፍሮች በመሆን የነዚህን ሐሳብ የተከተለ የስንቱ ቤት ፈረሰ፤ ገና ነፍሴ በሰማይ ቤት ዋጋ ታገኛለች በማለት ሥጋዬን ሳላለመልምና ሳላስደስት ለሰው በማካፈል የወንጌል ምርኮኛ ሆኖ መኖር ቂልነት ነውና፤ ከዛሬ ጀምሮ በነዚህ ሰዎች አማካይነት በርታ፤ ታጥቀህ ሃብታም ለምሆን ተነሳ።

እናንተም ምንም ቀደም ብሎ በብዙ ሰው ቤት የኖራችሁ፤ ለዚህ ስራ ልምድ ያላችሁ በመሆናችሁ ጊዜውና ዘመኑ ያፈራቸውን ወርቅ አልማዝ ዕንቁ ሌላም ልዩ ልዩ ነገሮች በየስራችሁ ተሰማርታችሁ አደራ የሰጠኃችሁን ሰው

ሃብታም እንድታደርጉልኝ ስለምናችሁ በተለይም አቶ ንፍገትን አጥብቄ የምለምንህ በምንም ዓይነት ገንዘቡን ወጪ እንዳያደርግ፤ መቆጠብን እንዲለምድ፤ ስስትን ከልቦናው ገብቶ እንዲቀመጥ አድርግ። ከዚህ በኋላ በጣም የከበረ ሰው ይሆናል" በማለት ለሁሉም በየስራቸው አደራ ሰጠ።

አቶ ምቀኝነትና ስስት ከበራፉ ላይ ቆመው ማንኛውንም ኃብት ወደቤት ከመግባት በስተቀር ወደውጭ በምንም አይነት እንዳይወጣ ጥብቅ ትዕዛዝ ሲሰጡ፤ በቦይ እንደተለቀቀ ውሃ ሃብቱ ይጎርፍ ይከማች ጀመር። በዚህ አይነት ለጥቂት ጊዜ እንደቆዩ ለዚህ ደርጃና ክብር ያደረሳቸው እግዚአብሔር መሆኑን ዘንግተው፡ በጉልበቴ፤ በአገልግሎቴ፤ በሰው ልጅነቴ፤ በእውቀቴ፤ በትምህርቴ ያገኘሁት ነው በማለት በስራቸው የሚተዳደርውን ታዛዥ ሰው ንብረት ወይንም መብት በመጠበቅ ፋንታ ለንብረቴ፤ ለእርስቴ ለበተሰቤ መተዳደሪያ፤ ባረጅም ለመጦሪያዬ ይሆነኛል በማለት በልዩ ልዩ ዘዴና ተንኮል በመንጠቅና በመግፈፍ ቤት ሲሰሩና ርስት ሲያስፋፉ በጠቅላላው ንብረታቸውን ሲያዳብሩ የእነሱ አካባቢዎች የሆኑ ግዋደኞችና ቤተ ዘመዶች - መልካም አደረግህ አዋቂ ነህ ጀግና ነህ በማለት ሲደልሉአቸውና በአፍ ጉቦ ሲያጋንናቸው ሥጋቸውን በማስደስትና በማልምለም ይኖራሉ።

## የሥጋ ዓለም ፍጻሜ

የሰው ልጅ ሥጋውን ለማለምለምና ለማስደስት በአየር ሲበር በምድርና በየብስ ሲሽከረከር ሲሮጥ ሲያራውጥ፤ በመቶ የሚቆጠሩ ቪላ ቤቶች እርስቶች፤ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገንዘቦች አጠራቅማለሁ በማለት መዋእለ ዘመኑን ለሕሊናው ጸጥታ ለመንፈሱ ዕረፍት ሳይሰጥና ለተቸገረ ወገኑ ሳያካፍል በሃብት ውቅያኖስ እንደተዋጠ ያ የሚያሳቅቅ ጻእረ ሞት በድንገት ሳያስበው ከተፍ ይላል።

ነፍስና ስጋውን አለያይቶ ሲገለው የሞቱ ብስራት በአካባቢውና በወዳጅ በዘመድ ሲሰማ ወዳጅም ዘመድም ጠላትም ሁሉም ወደሞተበት ስፍራ ይገሰግሳሉ። በደረሱም ጊዜ ይፈራበትና ይከበርበት ከነበረው አጥር ግቢ ውስጥ እስከ መኝታ በቱ ድረስ ማንም ሰው ሳይከለክላቸው ገብተው ወዳጅ ዘመዶቹ ለቅሶ ይጀምራሉ። ጠላትና ባላጋራዎቹም መሞቱን አረጋግጠው ይመለሳሉ።

ቤተሰቦቹና ወዳጅ ዘመዶቹ የልቅሶ አፍላ ይዘው ሲላቀሱ ዘመኑ ካስገኛቸው አዋቂ ነን ባዮች አንድ ሁለቱ ተነስተው ለቅሶውን ዝም በማሰኘት፣ ለምን ለቅሶ ብቻ ታለቅሳላችሁ? ይህ ሰው በድንገት ነው የሞተው ሳጥኑ አልተቆለፈ መኝታ ቤቱም ክፍት ነው። ምናልባት የገንዘብ ሰነዶችና ወርቅ ብር ጨርቅ ልብስ እንዳይባክን ሳጥኑና ቤቱ ተቆልፎ ይታሸግ የሚል ድምጻቸውን ሲያሰሙ ልጅም ሚስትም ወላጆችም ሕሊናቸው ወደ ንብረት ማሸግ ተመልሶ፣ መልካም ነው ይታሸግ ሲሉ የሚያሽጉ ሰዎች ይመረጡ ተብሎ በወቅቱ በስፍራው ከተገኙት ሰዎች ተመርጦ ለማሸግ ሲስማሙ ቀድሞ ንጉሥ፣ ጳጳስ፣ ጀግና፣ አዋቂ፣ ብልህ፣ የሚባለው ስሙ ተለውጦ "እሬሳ" የሚባል ስም ይሰጠዋል።

እሬሳ አውጡልንና እናሽግ ብለው ሲያመለክቱ ጥያቄያቸውን በመቀበል ከልጅነት እስከ ዕውቀት ዘመኑን ሙሉ ደክሞ ወጥቶ ወርዶ ከሰራው ቤት በደቂቃ ውስጥ አውጥተው ጥለው ቤቱን ያሽጉታል።

እሬሳው ከመኖርያ ቤቱ ሳይውል ሳያድር ወዲያው ወጥቶ ወደ መቃብር ይጓዛል፣ ከመቃብርም ሲደርስ 'ግባ ከመሬት' ተብሎ ተቀብሮ ወዳጅ ዘመድ ተሰናብቶ ሲመለስ ልጅ ነኝ ወይ አባት እናት ወይም ሚስት እስቲ በመቃብሩ ላይ ቀረት ብዬ ላልቅስለት፣ ያበላኝ ያጠጣኝ የነበረውን ውለታ በደቂቃ መዘንጋት የለብኝምና ቆይቼ ላልቅስ የሚል አንድ ሰው እንካን የለም፡ ከቶውንም እሱ በሞኝነቱ ነው የሞተው እኔ በብልጠቴ ቆይቻለሁና ከመቃብሩ ላይ ከሰው ተለይቼ ሳለቅስ የመቃብር ጋንኤል በጥፊ ቢመታኝስ? አይሆንም አልቀርም በማለት ወደ አደጋው ቤት ይመለሳል።

ከመቃብር ሲመለሱ እንደ ሃገር ልማድ ድንካን ተተክሎ ወይም ዳስ ተሰርቶ ወደ ቤት መልስ ይሆንና ከበራፍ ሲደርሱ የመቃብር ጉድጓድ የቆፈረውም ያልቆፈረውም ሁሉም እጃቸውን ታጥበው ከድንካኑ ገብተው ንፍሮ ቡና ቀርቦላቸው ይመገባሉ።

ቅድም እሬሳ አስወጥተው ካሸጉት የዘመኑ አዋቂ ነን ባዮች አንዱ ከመቀመጫው ብድግ ይልና "አንድ የማመለክታችሁ ነገር አለኝ፣ እሬሳ አስወጥተን ሣጥን ባሸግን ጊዜ በሳጥኑ ውስጥ ወርቅ ይኑር ወይንም ጨርቅ ያለውን ነገር አላየንም አልቆጠርንም በችኮላ ነውና የታሸገው አሁን ለቀስተኛው ሳይበተን ሰዎች ተመርጠው ቆጥረው ዘክረው ይታሸግ።

ምክንያቱም ሳይታይና ሳይቆጠር ቆይቶ ከወራሾቹ አንደኛው በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ በምስክር ደረጃ ቢያስጠራን ምን ብለን ልንመሰክር ነው? ስለዚህ አሁን መቆጠር አለበት ሲል፤ ኃደኛውም ይሄንኑ በመደገፍ ይናገራል። ለቀስተኞቹም ጥያቄውን በመደገፍ ሰው ምረጡ ተብሎ ምርጫ ይጀመራል።

በምርጫው ጊዜ ለማቹ ሚስት ረዳት ነኝ ባይ አንድ ሰው ብድግ ብሎ ምርጫ ሲደርግ ከጎና ጠጋ ይልና "እገሌን አትቀበይ ምክንያቱም ባልሽን ቀደም ብሎ በመሸታ በት እየወሰደ ገንዘብሽን ያስጨረሰው እሱ ነው፤ እንዲያውም ባትሰሚ ነው እንጂ በላይሽ ላይ ዲቃላ ወልዶ በነበረ ጊዜ የሚያሳድግበትና ምስጢሩን ሽፋኝ ነው።" በማለት ህሊናዋን በነገር ያዞረዋል፡ እስዋም በተጫነችው ነገር ተመራጮቹን ነቅፋ ለላ ሰው ትመርጣለች።

በወላጆችም በኩል እንደዚሁ ምርጫውን የነቀፋሉ፡ በጊዘው የነበሩት ሽማግሌዎች ሌሎች ሰዎች መርጠው እሸጉ ተከፍቶ ዕቃው ሲቆጠር፡ ሲዘከር የተገኘው ገንዘብ ለዕዳና ለልጆች ማሳደጊያ ለተዝካር ማውጫ ለመቃብር ቤት ማሰሪያ ደልድለው ሲያቀርቡ፤ ያ ከጎና የቆመው ረዳት ነኝ ባይ "ከልጅነት እስከእውቀት ያፈራሽውን ገንዘብ ድርሻሽን ተካፍለሽ በቅድሚያ ወስደሽ ተራፊውን የማቹን ድርሻ ለመቃብር ማሰሪያ ለልጆች ማሳደጊያ ለተዝካር ማውጫ፡ ለዕዳም የሚከፈል ከሱ ድርሻ መሆን አለበትና በዚህ እንዳትስማሚ ሲላት፡ ይሄንኑ በመመርኮዝ ለቤትሰብ ጉባኤ ታመለክታለች።

በወላጆች በኩል ደግሞ፤ ይሄንን ካመጣች ቀድሞ እስዋን ሲያገባ ለሰርግ መደገሻና ለጌጣጌጥ ተበድረን ያመጣነውን ገንዘብ እስከአሁን ያልተከፈለ ስለሆነ በተቀዳሚ ከጋራ ንብረታቸው መከፈል አለበት ብለው ሲያመለክቱበሁለቱ ወገን የተፈጠረውን ፀብ በመመልከት ነገሩን በሽማግሌ ለማየት ለእሁድ ቀን ተቃጠሩ። እስከዚአው ድረስ በቤቱ ውስጥ የሚገኙ ሳጥኖችና መኝታ ቤቱ ተቆልፎ ይታሸግ በማለት ተስማምተው አሽገውት ይበተናሉ።

አሁን ይህ ረዳት ነኝ ባዩ አንቺ ነገርሽ በሽምግልና ሊያልቅ ስለማይችል ይልቁንስ ጠበቃ ገዝተሽ ክስ ብታቀርቢ ይሻላል ብሎ በመከራት መሰረት ከጠበቃው ቤት ይወስዳታል። ከጠበቃው ቤት በደረሱ ጊዜ ለጠበቃው የባልዋን በደልና ምስጢር መዘርዘር ትጀምራለች፡

ጠበቃ፦ “ከነማን ጋር ነው የምትከራከሪው?”

ሴትዮ፦ “ከምዋቹ ከባለበቴ ወላጆች፡”

ጠበቃ፦ ነገሩን ለማካበድና ተቆርቓሪዋ ለመምሰል፤
“አዬ ባላጋራዎችሽ ኃይለኛና ጨቅጫቃ፤ ነገር ወዳድ ነገረኞች ናቸው፡ በምን አገናኘሽ?”

ሴትዮ፦ መቸም ለሴት ጠበቃዋ ወንድ ነውና፤ “ደሜን አውጣልኝ”

ጠበቃ፦ “ምን ትከፍሊኛለሽ? ነገሩ ከባድ ነው”

ሴትዮ፦ “መቼም ጥሬ ገንዘብ በእጄ የለኝ ታሽቓል እርስቱንም ሆነ ማንኛውንም ንብረት ተከራክረህ ስትረታልኝ ከድርሻዬ ግማሹን አካፍልሃለሁ፡”

ጠበቃ፦ “ታዲያ ለጊዜው ለቤንዚልም ሆነ ለማንኛውም ነገር የምንቀሳቀስበት ምንም ለዕለት የምትሰጭኝ ገንዘብ የለም?”

ሴትዮ፦ “የለኝም”

ጠበቃ፦ እየተበሳጨ፤ “ መቸስ ምን ይደረጋል የውል ተመልካች ይዘሽ ነገ ጥዋት እፍርድ ቤት ነዪና እንፈራረም”

በዚሁ መሰረት ተቃጥረው ይለያያሉ፡ በቀጠሮውም እለት ውሉን ፈጽመው የክሱን ፋይል ከፍታ ለባልዋ ወላጆች እና ለልጆችዋ መጥሪያ ይዛ፡ እየፎከረች ወደ ቤትዋ ትመለሳለች፡ መጥሪያውንም በልጆቹ በኩል ለምዋቹ ባልዋ ወላጆች ትሰጣለች።

ወላጆቹም በበኩላቸው ምክር ያደርጉና እስዋ እገሌን ጠበቃ ገዛች፤ እኛስ እገሌን ለምን አንገዛም? ጥብቅናውን እንደሆነ አገር የሚያውቀው ወፍ ከሰማይ የሚያወርድ፤ ዳኞች ንግግሩን የሚያዳምጡለት፤ ተመልካች ሕዝብ ይበል ይበል የሚሉለት አይደለም? ይሉና በበኩላቸው ወደ ጠበቃው ቤት ሄደው ተራቸውን ከጠበቁ በህዋላ የመጡበትን ጉዳይ ዘርዝረው ሲያስረዱት

የሴትዮዋን ክፋትና ተንኮል በመተንተን፤ ልጃቸውን በቂሙ የምትበድለውን ከነገሩት በህዋላ፦

ጠበቃ፦ "የመጣችሁበት ጉዳይ ከባድ ነው፡ ለምከራከርበት ዋጋዬን ስንት ነው የምትከፍሉኝ?

ወላጆች፦ "ለጊዜው የምንከፍልህ ጥሬ ገንዘብ የለንም፡ ታሸንፍ እንዲያውም ተከራክረህ በረታህ ጊዜ ከሚደርሰን ገንዘብና ሃብት ግማሹን ልንሰጥህ እንፈርምልሀ።" በዚህ ተስማምተው ከውል ቤት ሄደው ተፈራርመው ወደ ክርክሩ ይገባሉ፡

እንግዲህ የአንድ ሰው ንብረት የነበረው ከአራት ላይ ተከፍሎ በየምክንያቱ ገንዘባቸውን ሲወጡ ሲወርዱ ጨርሰው ብዙ ዘመን ሲከራከሩ ቆይተው፤ 'በግፍ የመጣ ገንዘብ በግፍ ይመለሳል' እንደሚባለው ምሳሌ ሁሉ የሽማግሌና ቤተሰብ ጉባዔን የስምምነት ውሳኔ አንቀበልም ብለው ከብዙ ዘመን በህዋላ ገላቸው አልቆ አጥንቱ ሲቀር እንዲታረቁ ይደረግና ያኔ የናቁትን ዕርቅ "ያወጣነውን ዕዳ ከሁለት አድርገን በየቤታችን እንግባ" በማለት ይስማሙና ወደየቤታቸው ይመለሳሉ።

ከዚህ ላይ ነው ነቢዩ ዳዊት የተናገረው የሚጠቀሰው፡ "ይዘግቡ ወኢየአምሩ ለዘያስተጋብኡ" ይሰበስባሉ ለማያውቁት ያከማቻሉ መዝሙር ፴፰ ቁጥር ፮
የሰው ልጅ በከንቱ ሕይወቱን ሙሉ ኃጢአት ከመስራትና ከንቱ ውዳሴን ከመከተል ይልቅ እግዚአብሔር በፈቃዱ ከአባቱ አብራክና ከእናቱ ማህጸን ደምና ስጋን አዋህዶ አጥንቱን ሰክቶ በአምሳሉ ፈጥሮ ወደዚህ ዓለም ያመጣው ኃጢአት መስራቱን ትቶ ደግ በመስራት ስሙን ለመቀደስ፤ ክብሩን ለመውረስ መሆኑን በአስርቱ ቃላተ ኦሪትና በስድስቱ ቃላተ ወንጌል የተጻፉት ትእዛዛት ይነግሩናል።

ከዚህም ሌላ በዚህ ዓለም ለመኖር የተወሰነ ወይም በኮንትራት የተሰጠው ዘመን የለም፤ በዳበሳ ለመኖርም የሚያጋጥመው ዘመን ፸ ፹ ቢበዛም ከ፺ እስከ ፻ውም ከ፻ ሰው ፩ ቢገኝ ነው፡ ለዚች እንደጥላ ለምታልፍ ዘመኑ እግዚአብሔር የሰጠውን ትዕዛዝ ረስቶ ሕገ ወጥ ተግባር በመከተል በጉልበቱ በብልጠቱ እያለ ሰጋውን በመከተል የነፍሱን መንገድ ሳያስታውስ በሀጢአት ውቅያኖስ እንደተዋጠና እጁን በሰው ደም እንደነከረ ነፍሱ በድንገት ጥሪ ተጠርታ ወደፈጣሪዋ ፊት ስትቀርብ፤ ለፈጸመችው ሕገ ወጥ ሥራ ጥያቄ

ሲቀርብላት የምትመልሰው ጠፍትዋት ስትቀባጥር ወደተወሰነላት ቦታ ትሄዳለች፡ በግፍ የተሰበሰበውም ገንዘብና ሀብት በግፍ ተመልሶ ይጠፋል ማለት ነው።

**አንባቢ ሆይ!**

እዚህ ላይ አተኩሮ መመልከት የሚገባን እያንዳንዱ ሰው ራሱን ከየት መጣሁ? አመጣጤስ እንዴት ነው? ከዚህ ያደረሰኝ ማን ነው? የሚል ጥያቄ ሲቀርብ መልሱ፦ እግዚአብሔር በፈቃዱ ካለመኖር ወደ መኖር፤ ከአራቱ ባህርያት ከእሳት ከውሃ ከነፋስና ከመሬት አዋህዶ አጥንትን ሰክቶ በእናቱ ማህጸን ዘጠኝ ወር ከ አምስት ቀን አኑሮ ወደ እዚህ ዓለም አመጣኝ፤ ከመጣሁም ሦሥት ዓመት በእናቴ እጅ ከ እሳት ከውሀ ከገደል ተጠብቄ የ እናቴን ጡት እየጠባሁ አደግሁ፤ ከዚያም ለትምህርት ወይንም እረኝነት እስከ ፲፯ ወይም ፲፰ ዓምቴ ድረስ ተመድቤ በ እግዚአብሔር ቸርነት በተሰጠኝ ዕድል ነጋዴ ወይም ወታደር፤ ገበሬ ወይም ካህን፤ ጳጳስ ወይም ንጉሥ ተመድቤ ለዚህ ክብርና ማእረግ በቃሁ የሚል መልስ ለጥያቄው ይመለሳል።

አስተዋይ ልቦና፦ "ዓሥርቱ ቃላተ ኦሪትንና ስድስቱ ቃላተ ወንጌልን ጠብቀህና አክብረህ ኖረሃል?"

የስጋ ምኞት፦ "አዎን"

አስተዋይ ልቦና፦ "ታዲያ ለምንድን ነው የባልንጀራህን ገንዘቡን፤ በሬውንም ሚስቱንም አትንካ አትመኝ ያለውን አልፈህ እርስቱን ወደ እርስትህ፤ ቦታውን ወደ ቦታህ ቀላቅለህ የወስድክበት? የገሌንስ ሚስቱን አባብለህ ያስከዳህበት? ስልጣንህንስ መከታና ጋሻ አድርገህ አይሰማም አይለማም ብለህ ለባለስልጣን እየነገርክ ያሳሰርከውና ያስደበደብከው?"

የስጋ ምኞት፦ "እርስቱን ጉልቱን ቦታውን ደብልቄ የወሰድኩበት ኑሮየን ለማሻሻል ነው፡ ደግሞስ ይሄ ዓለም ሲፈጠር ለውድድርና ለሽቅድድም ስለሆነ አንዱ ሰነፍ የተሰጠውን ሀብት እየሰራ ስለዓላማው በቦዝን የተቀመጠውን እርስትና ቦታ አልምቼ ኑሮየን በማሻሻል በተ ሰቤን ባስተዳድርበት ምን ነውር አለው?"

*አስተዋይ ልቦና፦ " እረ ለመሆኑ ጌታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በላብህ ወዝ ወጥትህ ወርደህ ብላ ያለውን አላነበብክም?" ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ከቁጥር ፲፯ እስከ ፲፱*

*የስጋ ምኞት፦ "እንብቤያለሁ፡ በላብህ ወዝ ብላ ያለው እኮ አንዱ ሰነፍ የተሰጠውን ሀብት ሳይሰራበት ጠፍ አድርጎ የሚያቆየውን መሬት ማልማት እኮ ሕጉን መጠበቅ እንጂ መጣስ አይደለም፡"*

*አስተዋይ ልቦና፦ "እግዚአብሔር ይሄን ዓለም ፈጥሮ የሰን ልጅ በዚህች ዓለም ላይ የተፈጠሩትን ፍጥረታት ማንኛውንም ለምግብ የተወሰኑትን እንዲበላና የበላይ ገዢነት ከተሰጠው ጀምሮ፤ ሀ/ ከአዳም እስከ ኖኅ ለ/ ከኖኅ እስከ አብረሃም ሐ/ ከአብረሃም እስከ ሙሴ መ/ ከሙሴ እስከ ዳዊት ሰ/ ከዳዊት እስከ ክርስቶስ ልደት ሸ/ ከክርስቶስ ልደት እስከ ፍጻሜ ዘመን በመሬት በባህር በተራራና በልዩ ልዩ ነገሮች ወስኖ በላይዋ ላይ የሰፈሩትን ሰዎች በቀለም በቓንቓ ለይቶ ፈጥሮ በመሪ በአስተዳዳሪ ወስኖ ሰጥቶአል። ከዚህም ዝቅ ብሎ የአንዱ ቤተሰብ እርስት ከአንደኛው ወገን አልፎ እንዳይወሰድ የተከለከለ ለመሆኑ አንዱ ሰው የወለዳቸው ልጆች መልካቸውና ቅርጻቸው ያንኑ ወላጃቸውን መስለው እንደሚወለዱና ወላጃቸው ሲሞት ርስቱን ጉልቱን ከሱ ለተወለዱት ልጆች ብቻ ትቶ እንደሚሄድ ሁሉ፤ ዲቃላ ልጅ ከመካከላቸው ቢገኝ እንካ ከዕርስቱ እንዳይገባ ወስኖት እንደሚሞት በግልጽ ይታወቃል፡ ከዚህ አልፎ የሰውን መብት ጠፍ አድርጎታል ተብሎ ወደ መብቱ ማድረግና መውሰድ በህግ ፊት ያስወቅሳል ያስቀጣል።"*

*የሥጋ ምኞት፦ "ከአብርሃም እስከ ምጽአት ድረስ የሰው ልጅ በውድድር ያንዱን አንዱ እየነጠቀው መኖሩን ታሪክ ይነግረናል፡ እኔም ከሰነፉ ሰው ላይ ጠፍ አድርጎ ያኖረውን ሃብት ወስጄ ባለማና ባስፋፋ የሚያስነውረኝ ነገር ስለሌለ ወስጃለሁ፡ ደግሞስ ይህች ዓለም አሸብርቃና አምራ የምታያታና የሰው ልጅ በምድር መሽከርከርን በሰማይ መብረርን ወደመሬት ጠልቆ ወደሰማይ ርቆ ለመገስገስ የቻለው ሰነፍ የቦዘነውን መሬት በማቅናት አላዋቂውን ሕዝብ አዋቂው ሕዝብ በማስተማር አይደለም፡ ሀብታም አዋቂ የሚያሰኘው? ስለዚህ ለመከበርና ሀብታም ለመሆን ያስፈልገኛል።"*

***አቶ መንፈሳዊና አቶ የስጋ ምኞት በአቶ አስተዋይ ልቦና ዳኝነት ችሎት ፊት ቀርበዋል።***

*አቶ መንፈሳዊ፦ "እግዚአብሔር ያሳይዎ፤ አምላክ ያመልክትዎ፡ አቶ አስተዋይ ልቦና በጥሞና ይስሙኝ፡ አቶ የስጋ ምኞት ከዚህ በላይ ያመለከተውን ሰምተዋል፤ በእኔ በኩል የሚከተለውን አስረዳልሁ፤*

*ነገር በምሳሌ ጠጅ በብርሌ እንደሚባለው ሁሉ፤ ሳይፈሩ እውነት ሳይጠራጠሩ ዕምነት፤ ለሰው ሞት አነሰው፤ በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ፤ ደስታ በሽታ፤ ሳይቸግር ጤፍ ብድር፤ ከነገሩ ጠም እደሩ፤ የማታ ማታ እውነት ይረታ፤ ካልዘለሉ አይሰበሩ፤ የሴት ሌብ ወንድ ሊበላ፤ ታሞ የተነሳ እግዜርን ረሳ፤ ሕግን መናቅ በሽቦ መታነቅ፤ ሳል ይዞ ስርቆት ቂም ይዞ ጸሎት፤ አተርፍ ባይ አጉዳይ፤ ሰው ለአማኙ እግዜር ለለማኙ ሞኝ፤ የእለቱን ብልህ የአመቱን፤ በፊት እውቂኝ በኃላ ደብቂኝ፤ የድሃ ብድር አይውል አያድር፤ ሰው ወጣኝ እግዚአብሔር ፈጻሚ፤ በገቡበት አይወጡበት፤ ስንቅና አባይ እያደር ይቀላል፤ ወዳጅ ሲከዳ ይቀላል እዳ፤ ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም፤ ክርና ነገር ባጭር፤ ነገርን አዳምጦ እህልን አላምጦ፤ ከተሰቀለ አይወርድ ከተሳለ አይበርድ፤ እንደተባለው ሁሉ የሥጋ ምኞት በዚህ ዓለም ላይ የፈለገውን ሲያወጣና ሲያገባ ሲበላ ሲጠጣ የቁርጥ ፍርድ ነፍስና ሥጋ የሚለይ ጻእለ ሞት ጥርሱን አግጥጦ ዓይኑን አፍጥጦ ከተፍ ብሎ፤ 'ነፍስ ሆይ፤ ነይ ውጭ' ብሎ ከማህደረ ሥጋዋ ሲያስውጣት አጅሬ ሥጋ ሲበላ ሲጠጣ ኖሮ እስኪ አንድ ምዕራፍ ልከተልሽ ሳይል እንደ ድንካን ወይንም እንደ እባብ ግልፋፊ ውልቅ ብሎ ይቀራል፡ ከምድር መከረኛይቱ ነፍስ በሥጋ ምኞት የተሰራው ሥራ በሰውነት ላይ ተለጥፎ በነጻእረ ሞት አጃቢነት ከጭራ በቀጠነ ግራ ቀኙ እሳት በሚነድበትና በሚይስፈራ መንገድ አቓርጣ ከፈጣሪዋ ፊት ደርሳ እጅ ስትነሳ፤*

*ፈጣሪ፦ "ምነው ነፍስ ሆይ፤ በደልሺኝ ትእዛዛቴን ሳታከብሪ ጥፋት ሰራሽ?*

*ነፍስ፦ "ኧረ ባለማወቅ ነው፡ በአንተ ፊት ቀርቤ የምቀጣ የምወቀስ መሆኔን ባውቅስ ይሄንን ባላደርገውስ ነበር"*

*ፈጣሪ፦ " እንዲህ እንዳትይ መምህራንን ቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍትን ሰጥቼሽ ከዚህም ሌላ ክረምትና በጋን ፀሐይና ጨረቃን ሳፈራርቅ፤ ዝናምን ሳዘንም፤ አፍላጋትን ሳፈራርቅ፤ ከሰው ለየሁሽ?*

*ስትባል አጅሬ ሥጋ በዚህ ዓለም ሲበላ ሲጠጣ ሲሮጥ ኖሮ አዚሁ ከመሬት ቀርቶ በመቃብር ሆድ ክትት ብሎ ይቀራልና፦ ስለዚህ የሥጋ ምኞት*

*የነፍስን መከራና ስቃይ አስታውሰህላት ትእዛዛቶችን አክብረህና ጠብቀህ ብትኖር ይሻልህ ነበር በማለት ንግግሬን አቆማልሁ።”*

## *የአቶ ሥጋ ምኞት መልስ*

*አቶ አስተዋይ ልቦና እግዚአብሔር ያሳይዎ፤ አምላክ ያመልክትዎ፤ አቶ መንፈሳዊ ስንፍና የተመላበት አነጋገር ነው ያመለከተው። ምክንያቱም ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል፤ እንደሚባለው ሁሉ አምላክ ሲሰጥ ምክንያት ያዛል፤ በትንሽ ያልታመነ በብዙ አይታመንም፤ እጅግ ሞኝነት ያደርሳል ከሞት፤ ለሰባቂ ጆሮ አትስጠው፤ አንድነት ያለው ጠላቱን ያሸንፋል፤ መልካም ሚስት ለባልዋ ዘውድ ናት፤ ሰምቶም ዝም አይቶም ዝም ወይ የምድር ሰው በሆድ ያለ አይነቅዝም፤ የአፍ ብልሃት ጌትነት የእጅ ብልሀት ባርነት፤ ነገረኛ ናቸው በጣም ፍሩአቸው፤ እነ ዘንድ ሆነህ ባየሀው፤ ገንዘቤ አትውጪ ከቤቴ፤ የዘነጋ በቱን ዘጋ፤ የተከፋ ተደፋ፤ ከራስ በላይ ንፋስ፤ ገባር የአህያ ግንባር፤ አበልጅ አትቁም ከደጅ፤ ዘንዶ የዳገት በረዶ፤ የሰውን ነገር አለመናገር፤ አታላይ ጉድኃድ ዘላይ፤ ቢሄዱ አገር ቢተኙ ነገር፤ ምናልባት ቢሰበር አናት፤ ስንተዋወቅ አንተናነቅ፤ በአንድ ራስ ሁለት ምላስ፤ ተለማማጭ አልማጭ፤ የቸኮለ አፍሶ ለቀመ፤ የራበው ሰው ይጠግብ አይመስለው፤ ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ፤ ስሙን ለሰው አወረሰው፤ አላዋቂ ወሬ ጠያቂ፤ እንደገና ይሞታል በገና፤ የፈሩት ይደርሳል የጠሉት ይወርሳል፤ ረጅም ባይፈራ አጭር ባይኮራ፤ ይሆን ቢሆን ዝሆን ይበላ ቢሆን፤ ስትግደረደሪ ጦም አትደሪ፤ የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው፤ ካልታረደ ስባቱ ካልተሞከረ ብልሃቱ፤ ባለፀጋ በሀብቱ ድሃ በጉልበቱ፤ የወፍ ወኑ የሰው ሆዱ፤ ውሻ ከሸሹለት ልጅ ከሳቁለት፤ ትጉል ጥንቆላ የሰው ልጅ መላ፤ ብጥለው ገለበጠኝ፤ ውሻ በበላበት ይጮሃል፤ ገንዘብ ከጅ ከወጣ ያመጣል ጣጣ፤ ልጅ ታርጣጣ እህል ከዘበጣ፤ እኛ በሃገራችን ዳቦ ነው ፍሪዳችን፤ የሴት አመዳም የአሮጌ ሆዳም፤ ሰው ከዘመዱ አህያ ካመዱ፤ ያለአንድ የላት ጥርስ በዘነዘና ትነቀስ፤ የሮጠ አመለጠኝ የበላ በለጠኝ፤ ሥራ ያጣ ገበሬ ይሞታል በሰኔ፤ የበላ ዳኛ የወጋ መጋኛ፤ ለሂያጅ የለውም ወዳጅ፤ ጥቂት ሥጋ እንደመርፌ ትወጋ፤ ቀጥኜ ቢያየኝ ጅማት ለመነኝ፤ ሥጋ ለጥጋብ አጥንት ለትካዜ፤ አለኩያ ጋብቻ ቆይ ብቻ፤ ሆድ ለባሰው ማጭድ አታውሰው፤ ሆድና ግንባር አይሸሸግም፤ ጥሩ ወዳጅ ጠላት ይሆናል፤ ጠጅ የወረት ወዳጅ የበላ ዕለት፤ የበላ ቢያብል ገላው ይናገር፤ ሰው በአገሩ ዘፈን በትብብሩ፤ ሳይረቱ አይበረቱ፤ ወዳጅ ለችግር ዕለት፤ ከአልሰሩ አይገኝ ብሩ፤ የሮጠ አመለጠ የዘገየ ትለየ፤*

በወረት ኮሶ ይጣፍጣል፤ የቸገረው እርጉዝ ያገባል፤ የቀበጡ ዕለት ሞት አይገኝም፤  ተግደርዳሪ ጦም አዳሪ፤ አባይ ለእለቱ ደስ ያሰኛል፤ ባለጋራ ያለው ዕንቅልፍ የለውም፤ ባለቁርጥ አደንግጥ፤ ባለጌ ገንዘብ አያከብርም፤ ባለነገር ከቤት ጠርቶ ከችሎት፤ ባልቤት ካልጮሀ ጎረቤት አይረዳም፤ አባት ሲታማ ልጅ አይስማ፤ ከሰጪው አሰጪው፤ ባትዋጋ እንካን ተሰልፍ ከመልካ፤ ከሆነ ወዲያ ንዴት መሸበት፤ ከመቸገር ሰርቆ ማደር፤ ከሩቅ ዘመድ የቅርብ ጎረቤት፤ ሰው ያለአገር መሬት ያለዘር፤ ሥራ ከመፍታት ልጄን ማፋታት፤ ሰርገኞች መጡ ብቅል አስጡ፤ ሰነፍ ሳል ያበዛል፤ ሰው በወሬ ዱቄት በሙሬ፤ ከስብ ስም ይሸታል፤ ቢከማች ዕዳው የአንቺ፤ ብዙ መላ እምብዛም አይበጅ፤ በዳቦ ላይ ሙልሙል፤ የደሃ ጉልበቱ በገበያ ያልቃል፤ በዝና የለም ጤና፤ ሰይጣን ለወዳጁ ድርብ ነው አሉ፤ እንደተባለው ሁሉ ያላግባብ ነው ያመለከተው።

## የአቶ አስተዋይ ልቦና አስተያየትና ፍርድ እነሆ!

አቶ የሥጋ ምኞትና አቶ መንፈሳዊ (ተስፋ) ያቀረባችሁትን አመለካከት አንድ በአንድ አዳምጫለሁ።

ወይ የምድር ሰው የሰማዩን ባይቀምሰው፤ከስስታም አንድ ይወድቀው አንድ ያንቀው፤ ዛር ልመና ሳይያዙ ገና፤ ከተያዙ ብዙ ነው መዘዙ፤ ከሃገር ተስፋ ውሃ ጠፋ፤ አንድ ቀን ቢስቱ ዓመት ይፀፀቱ፤ ሲበዛ ማር ይመራል፤ ገበጣ ለአዋቂ ወሬ ለጠያቂ፤ መተው ነገሬን ከተተው፤ ካልጠገቡ አይዘሉ፤ ዕድል ተርታውን ዕጣ ፋንታውን፤ እርጥቡ እሬሳ ደርቁን አስነሳ፤ ሴትና ፈረስ ያቀርቡለትን ይቀምስ፤ አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ፤ ለሞት የለውም መድሃኒት፤ ሆደ ሰፊ ነገር አሳላፊ፤ እግር ከሸሸ ልብ ሸሸ፤ በአዋቂ ፊት መናገር መታገም፤ ይግቡ በደጃፉ በአጠገቡ ሰው የለም ይላሉ፤ በደግነት ተቆረጠ አንገት፤ በጅ አግብቶ ቁጣ፤ ክፉ ያስከፋል ጎሽ ያገለግላል፤ ከባለቤት ወዲያ መስካሪ ከአምላክ ወዲያ ፈጣሪ፤ ዞሮ ከቤት ኖሮ ከመሬት፤ የማይቀር ነውና፡-

ትክክለኛ ፍርድ አለ ከላይ ቤት
ሥጋ ትቅምተኛ ነፍስ ወደ  እሳት
የማይገባ ነው በዚህ መሳሳት
ሕጉን መጠበቅ ነው ጎቀኛው እውነት
መደሰት ብቻ ነው የሥጋ ምኞት

ሥጋ የወደደውን ሩጦ ማርካት
ተውጦ መቅረት ነው በመቃብር ቤት
እነ አፈር ፈታውራሪ ከያዙ በኃላ
መመለሻ የለም አይገኝም ገላ
ደብዳቤ ሲደርሳት ከሞት አበጋዝ
ነፍስ አትልም ልዋል ስንቄንም ልያዝ
መላእክት ጽልመትና መላእክተ ብርሃናት
ከበው ሲያክለፈልፉ ቶሎ በቅጽበት
ትደርሳለች ወዲያው ከፈጣሪ ፊት
ሰግዳም ትቆማለች ለሦሥት ጊዜያት
ጥያቄ ይቀርባል ከግርማው ባለቤት
መቀበጣጠር ነው እንዲያው መወትወት
ሰባት ቀን አዙራት መልካሙን ገነት
በስምንተኛው ቀን ይዘሃት ሲኦል ውረድ
ነፍስና ሥጋዋን አዋህጄ እስክፈርድ
ብሎ ያዛቸዋል ግርማ መለኮት
ይሄን ተቀብላ ስትሄድ ወደ ሲኦል
ጥልምያኮስ በደስታ ይላል ዕልል ዕልል
ሸኙአት መላእክተ ብርሃናት በሃዘን በሮሮ
ጊዜ እማይለውጠው ዋ ስንቱ ተነግሮ
የመከራው ብዛት በዚህ ቀን ይሻላል የማይባልበት
የታልቁ ንጉስ ፍርድ አድልዎ የለበት
በመንግስቱ ሽረት በዕድሜው ሞት የለበት
ቁርጥ ፍርድ መስጫው የፍርዱ ቀን ሳይደርስ
እዚሁ እያሉ ነው በንስሓ መመለስ
በጥሪ ደብዳቤ ተይዞ ሥጋ ሳይበሰብስ
ሕጉን መጠበቅ ነው ለመንግስተ ሰማያት ውርስ
ስል ፍርዴን እሰጣለሁ ለሥጋ ብስብስ

ይኽኔ አቶ የሥጋ ምኞት "አቶ አስተዋይ ልቦና ፍርድዎ ቀጠነኝ፤ ወደ አቶ እንደጊዜው ይግባኝ ብያለሁና ግልባጭ ይስጡኝ ሲል አመለከተ፡ አቶ አስተዋይ ልቦናም ግልባጩ ይሰጠው ብሎ አዘዘ።

አቶ የሥጋ ምኞትም ግልባጩን ከይግባኝ ማመልከቻ ጋር አያይዞ አቶ እንደጊዘው ፊት ቀረበ። የማመልከቻውም ፍሬ ቃሉ እንዲህ የሚል ነበር፦

“ለክቡር አቶ እንደጊዜው፡ በአቶ አስተዋይ ልቦና ዳኝነት የተፈረደብኝን የግፍ ዳኝነት የግብር አበሮችዎን እነ ምቀኝነትን፤ ተንኮልን፤ ንፍገትን፤ ስስትን፤ ዝሙትን፤ ኩራትን፤ ቅናትን፤ ይዘው በኮሚሲዮን መርምረውና አጣርተው እውነተኛውን ፍርድ እንዲያዩልኝ ሳመለክት የነገሬም መነሻና መድረሻ ይኸ ነው፡ እግዚአብሔር መቶ ነገደ መላእክትን ፈጥሮ ሲሰወር ‘ማን ፈጠረን? ማን ፈጠረን?’ ሲባባሉ ቀናተኛው የግብር አባቴ ዲያብሎስ እኔ ነኝ የፈተርኳችሁ ብሎ በድፍረት ሲናገር የፈጠረን እሱ ነው ያሉና የተጠራጠሩ ብዚህ ዓለም ላይ እግዚአብሔር ክብሩን ለመወረስ ስሙን ለመቀደስ ሲል ለሰው ልጆች የሰጠውን ሃብትና ጸጋ እንደ እነ አብራሃም በማብላትና በማጠጣት ትሩፋት በሚሰሩት ጊዜ ተንኮለኞች አጋንንቶች የግብር አበሮች ሆነው የተገኙ ሰዎች ሁሉ ተድላ ደስታቸውን ትተው በሞት ጥሪ አማካይነት ከጭራ በቀጠነ መንገድ ሄዶ ከፈጣሪ ፊት የሚናገሩት አጥቶ ከመቀባጠር ይልቅ ቀድሞ በአሪቱ ዓሥርቱ ቃላት ህዋላም በሓዲስ ብስድስቱ ቃላተ ወንጌል የተጻፈውን ጠብቆ የተሰጡትን ሀብት ለለላው አካፍሎ ትሩፋት ሰርቶ መገኘት ይሻላል የሚለውን የተከተለ ድህነት ውጦት ይታያል።” የሚል ነው

አቶ እንደጊዜውም የቃለ ጉባዔውን ፀሐፊ ጠርቶ በል እንካ ይኼንን ማመልከቻ አይተህ እዚያ ላይ የተጠከሱትን ሰዎች ለማክሰኞ ቀን ይጠሩና ጉባዔ ተከፍቶ ባላጋራው አቶ መንፈሳዊ ምኞት  መጥሪያ ተጽፎለት ይቅረብ ሲል አዘዘ።

በቀጠሮው እለት በስም የተጠቀሱት አባሎች ባሉበት ግራና ቀኝ ቀርበው ክርክሩ ቀጠለ፡ የይግባኝ ባዩ ማመልከቻ ተነቦ የይግባኝ መልስ ሰጭውም ከተነበበ በህዋላ አት ንፍገት አቶ መንፈሳዊ ተስፋን እንዲህ ሲል ጠየቀ፦ “ኧረ ለመሆኑ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ፈጥሮ በዚህ ዓለም ላይ ሲይስቀምጥ ግዛ፤ ንዳ፤ ብላ፤ ጠጣ ሲል በሰጠው ትእዛዝ መሠረት አንድ ሰው ወጥቶ ወርዶ ነዶ በርዶ ያገኘውን ሀብት በስንፍና ለደካማ ሳይሰጥ ገንዘቡን አስከብሮ አንከባክቦ አጠራቅሞ በሰው ዘንድ ባለጸጋነቱ ታውቆለት፤ እገሌ ሀብታም ነው እህሉንና ብሩን በወለድ ያበድራል በወለድም የተበደርው ሰው የወሰደውን ገንዘብ ባልመለሰ ጊዜ መሬቱን የከተማ ቦታውን በዕዳው እያስቀረ ብዙ የከተማ ቦታና ዕርስት አስፋፍቶ በብርም በኩል ሚሊዮኔር የሚል ቅጽል ስም ከማግኘቱም በላይ ሥጋውን አለምልሞ በሰው ዘንድ መፈራትና መከበርን የሚያገኘው በዚህ አይደለም? አንተ የምትለው

የወንጌልን ቃል ተከትለህ ድሃ ሁን በሰው ዘንድ ተዋርደህ ኑር ነው፡ ይሄ አይገባም። ብሎ ንግግሩን ያቆማል፡

አቶ ተንኮል በበኩሉ ብድግ ብሎ ኧረ ለመሆኑ ስማ ልንገርህ ዲያብሎስ በእባብ ተመስሎ ሔዋንን አስቶ ዕፀ በለስን ባያስበላት ኖሮ ይህች ያለንባት ምድረ ፋይድ ዛሬ አጊጣ አሸብርቃ እንደምታያት ትገኝ ነበር? ደግሞስ ይህች ዓለም ከተገኘች ወዲያ የሰው ልጅ አንድ መጽሐፍን ተከትሎ ከመሄድ የአንዱን ደካማ መንግስት ጉልበታሙ ነጥቆ ባይወስድ አንድ ሰነፍ የተሰጠውን ዕርስትና ጉልት ባለመስራቱ በመሬት ላይ የሚገኘውን ወርቅና አልማዝ ተደብቆ ሊቀር የነበርውን እኔ ተንኮል ብድግ ብዬ በመቃወም ልባለ ጉልበትና ሃብታም እየነገርኩ እያስነጠቅሁ ባላደርግ ኖሮ መቸ ወርቅና አልማዝ በሰው ዘንድ ይገኝ ነበር? አንዱስ ሃብታም ደካሞችን በስልጣኑ እንዲበድላቸውና እንዲገድላቸው ባላደርግ የሰው ልጅ በሰላም እየኖረ ድህነት ይወርሰው አልነበርምን? ለደግ ክፉ ባይኖር ኖሮ መቸ አንዱ ላንዱ ይገዛ ነበር አሁንም የሰነፍ አነጋገርና አስተሳሰብ ስልሆነ በአቶ የሥጋ ምኞት የይግባኝ መደገፊአ ማመልከቻ ላይ የተጠቀሰው የአበቱታ ቃል የሚደገፍ ነው ሲል ንግግሩን አቆመ።

አቶ ስስት የሚባለው በተራው ተነስቶ እንዲህ ሲል ለመንፈሳዊ ተስፋ ጥያቄ አቀረበ፡- አቶ መንፈሳዊ ተስፋ አንተ በአስተዋይ ልቦና ዳኝነት ላይ የስንፍና ክስ አቅርበህ ያለአግባብ አስፈረድክበት አረ ለመሆኑ እኔ የስስት ጌታ ባልኖር ኖሮ ቸርነት የሚባለው ሐሳበ ደካማ እግዚአብሔር በላብህ ወዝ ጥረህ ግረህ ብላ ያለው ቀርቶ አንዱ ቁጭ ብሎ ቂጡን ሲያለፋ አያ አጅሬ ቸርነት ቤትህ የሃብታም ቤት ሁልጊዜ ግብር ሁልጊዜ ችሮታ ነው እያለ በአነጋገር ስልት እያታለለ የስንቱን ቤት ያደኸይ ነበር፡ እኔ የስስት ገታ ከተገኘሁ ወዲህ ግን የኑሮን ዘዴ በማስፋፋት ቁጠባን በማወቅ ብዙ ዕርስቶች፤ የከተማ ቦታና ቤቶች በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በባንክ በማጠራቀሜ ዛሬ እንደምታየው ሰማይ ጠቀስ ፎቅ ሰርቼ ብዙ ቪላዎች አከማችቼ ዕድሜ ልኬን ሙሉ ድህነት የሚባለውን ተባይ ከቤቴ ሳላስገባ እነሆ ተከብሬ እኖራለሁ፡ ዘመድ ወዳጅም ሊጠይቀኝ ቢመጣ ብላ ከማለት ተቆጥቤ ብዚህ ዓይነት ሀብታምና ስስታም የሚል ቅጽል ስም አትርፌ እኖራለሁ፡ ስለዚህ የአንተ ሃሳብ የድህነት ተገዢ ልታደርገኝ ስለሆነ በፍጹም አልቀበልምና ዶሰህ ይሰረዛል ሲል ንግግሩን አቆመ።

አቶ ዝሙት በበኩሉይ ተነስቶ እንዲህ ሲል ተቸ፦ አቶ መንፈሳዊ ተስፋ ጥንቱን እግዚአብሔር ለአዳም በሰጠው ትእዛዝ ላይ ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙልዋት ሲል የሰጠው ትዕዛዝ የሚከበር ስለሆነ ዓይኖቼ ያይዋትን ልቤ የተመኛትን ቆነጃጅት ሁሉ በመገናኘት ሕጉን ከመጠበቁም በላይ በልቤ ያገኘሁትን ገንዘቤን በቁም ነገር ላይ በማመንዘር በማዋሌ እደሰትበታለሁ አንተ አሁን ምን ሰራህን የሚል ጥያቄ ቢቀርብልህ ከቶ ምን ልትመልስ ነው? አሁንም ክስህ ይሰረዛል ሲል ተናገረ።

## የይግባኙ ፍርድ

አቶ መንፈሳዊ ምኞት በፊት በአቶ አስተዋይ ልቦና ችሎት ያስፈረድከውን ፍርድ አንድ በአንድ ተመልክቸዋለሁ፡ አሁንም በእኔ ችሎት ላይ የግብር አበሮቼ የተቹትን አንድ በአንድ ሰምብቻለሁ ስለዚህ አቀራረብህና የክስ አመለካከትህ በጭራሽ ለዚህ ዓለም ኑሮአችን ተስማሚ ባለመሆኑ አቶ አስተዋይ ልቦና የፈረደውን ፍርድ ለውጬ ለአቶ የሥጋ ምኞት የፈለገውን እንዲፈጽም አጽንቻለሁ። እስከ አሁንም ባጉላላህበት የወጣ የወረደበትን ኪሳራ ችምር ትከፍላለህ ስል ፈርጃለሁ።

አቶ መንፈሳዊ ምኞት የአቶ እንደጊዘውን ፍርድ አሰማ በኃል ይግባኝ ብሎ አቶ መቆየት ወደሚገኝበት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፀፀት ከተማ ይግባኙንና የይግባኝ ማመልከቻውን ይዞ ቀረበ፡ ፍሬ ቃሉም ይህ ነበር፦

*ለክቡር አቶ መቆየት*
*የጠቅላይ ትዕግሥት ፍርድ ቤት ዋና ፕረዚዴንት*
*ፀፀት ከተማ*

*ክቡር ሆይ፡*

*እግዚአብሔር ያሳይዎ አምላክ ያመልከትዎ። አመልካቹ እኔ መንፈሳዊ ምኞት እና ባላጋራዬ አቶ የሥጋ ምኞት የአንድ እናትና አባት ልጆች ስንሆን በግብር እንደ ዘይትና ውሃ የማንዋሃድ ሆንን፤ ምክንያቱም አቶ የሥጋ ምኞት ዓይኔ ያየውን ልቤ የተመኘውን ማናቸውንም ነገር ልቀመስ ልደሰት ባይ ሆኖ በማኀደረ ሥጋ የተዋሐደችውን ረቂቅ ነፍስ ምንም የአንድ እናትና አባት ልጆች ብንሆን ገና ነፍስ በሰማይ ሳይ ወጥታ መከራና ደስታ ትቀበላለች ማለትን የመጽሐፍን ወሬ ብሰማ አልቀበልም። እዚሁ በሥጋዬ ተደስቼ በተሰጠኝ ጉድጓድ ከነፍስ ተለይቼ እገባበታለሁ በማለት እኔን የመከራ ጥንስስ እየጠነሰሰ አንተው ግጠህ*

ውጣው እያለ ሊያስቸግረኝ በአቶ አስተዋይ ልቦና ችሎት ላይ ክስ አቅርቤ አስፈርጄበት ወደ አቶ እንደጊዜው ይግባኝ ብሎ በትክክል የተፈረደልኝን ፍርድ አስገልብጦብኝ እነሆ ወደ እርስዎ አቶ መቆየት ዘንድ ግልባጩን ይዤ ቀርቤያለሁ፡ የሥራ ጓደኞችዎን አቶ ማጣትን፤ አቶ ውርደትን፤ አቶ ንስሓን ይዘው በይግባኝ ማመልከቻዬ ላይ እንደገለጽሁት ሁሉ ያለአግባብ እውነተኛው ፍርድ ተለውጦ የተፈረደብኝን ፍርድ በታላቁ ጌታ ዳኝነት ላይ ቀርቤ ቁርጥ ፍርድ ተፈርዶብኝ ገሃነም ከሚባለው ታላቅ ወህኒ ቤት ገብቼ እሳት እንዳልማተረው ድማት ለመቃጠል በፊት አቶ የሥጋ ምኞትን አስጠርተው የግብር አበሮቹን ኩራትን፤ ምቀኝነትን፤ስስትን እና እነዚህን መሰሎች ጓደኞቹ ጭምር ቀርበው ለስስት አቶ ቸርነትን፤ ለኩራት አቶ ትህትናን፤ ለምቀኝነት አቶ ደግነትን፤ ለራሱ የሥጋ ምኞት መምሬ ንስሃን ሰጥተው ለትንሽ ቀን በጸጸት ከተማ ባለው ታላቁ የንስሐ ትምህርት ቤት ገብቶ እንዲማር ያደርጉልኝ ዘንድ በትሕትና አመለክታለሁ፡፡ ሲል መንፈሳዊ ምኞት አመለከተ።

አቶ መቆየት ከዚህ በላይ የተጻፈውን ማመልከቻ ንባብ አዳመጦ በስም የተጠቀሱት የሥራ ጓደኞቹ ባሉበት መዝገቡን ከመረመረ በኃላ በጣም ቅሬታ እና በደል ያለበት ስለሆነ አቶ የስጋ ምኞት ይጠራ ተብሎ የይግባኝ ማመልከቻው ግልባጭ ተልኮለት መልሱን ይዞ ይቅረብ ተብሎ ቀጠሮ ተሰጠው። በቀጠሮው ዕለት አቶ መንፈሳዊ ምኞትና የሥጋ ምኞት ተቃርበው መዝገቡና የሁለቱም ማመልከቻ ተነበበ፡፡

ዳኛው አቶ መቆየት፦ አቶ የሥጋ ምኞት፤ የአንድ እናት እና የአንድ አባት ልጆች አይደላችሁም?

የሥጋ ምኞት፦ አዎን ነን

አቶ መቆየት፦ ታዲያ ለምንድን ነው የናትህ ልጅ ተንኮል የሚባለውን የዲያብሎስን ግብር አትከተል ቢልህ አልቀበልም ብለህ በተንኮል ጓደኛህ አጋዥነት ሥጋየን በተድላና በደስታ አለመልማለሁ ነፍሰ የት እንደምትደርስ አላውቅም አልጠየቅም የምትለው?

የሥጋ ምኞት፦ ጌታዬ አሁንም አላውቅም ብያለሁ፡ ምክንያቱም በዓይኔ የማየውን ተድላና ደስታ ለቅቄ በዓይኔ የማላየውን በሰማይ ቤት ተድላና ደስታ አያለሁ ብዬ አላምንምና በዚሁ በመሬት ሳለሁ መደሰት እፈልጋለሁ

አቶ መቆየት፦ በሰማይ ቤት ደግ የሰራ መንግስተ ሰማያት ገብቶ ዘለዓለም መደሰቱን በምድር ክፉ የሰራ በሰማይ ገሃነም መግባቱን በብሉይ ኪዳን በ፲፰ቱ ነቢያተ መጻህፍት፤ በዳዊት፤ በሄኖክ፤ በወንጌል፤ በሃዋርያቶች ሌላም

ብዙ ሌሎች የክርስቶስ ቤተ ሰቦች በየጊዘው መንፈስ ቅዱስ የገለጸላቸውን በማስታወሻ እየጻፉ የዓይን ምስክርነታቸውን እያበረከቱ ሄደዋል፡ በነዚሁ መሰረት በአይን የሚታዩ ቤተ ክርስቲያኖችና ካህናቶች በየሳምቱ ቅዳሜ እና እሁድ በሌላውም ቀን ያስተምራሉ፡ ስለዚህ ፍርድ ከመስጠታችን በፊት ቀኖና የሚባለውን ባልደረባ ሰጥተንሃልና ከእርሱ ጋር ንስሓ ከሚባለው ገዳም ገብተህ ማጣትን፤ መዋረድን፤ መለመንን፤ መቸገርን፤ አራቱን መደብ አጥንተህ እንድትመለስ ይሁን። ብለውት ቀጠሮ ተቀብሎ ወደ ንስሐ ገዳም ጉዝውን ቀኖና ከሚባለው ባልደረባ ጋር ቀጠለ።

በገዳሙ ውስጥ ትምህርቱን ሲያጠና ቆይቶ ሲመለስ ጓደኞቹ ንፍገት፤ ኩራት፤ ተንኮል ከድተውት በሥፍራቸው አቶ ፀፀት፤ ድህነትና ትሕትና ተተክተው አገኛቸው፡ ለጊዜው የሚያውቃቸው ሰዎች ለቀው እንግዶች ሰዎች በማግኘቱ በነገሩ እያዘነ ቆይቶ እሁድ ቀን ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሲሄድ እግሩ የተቆረጠ፤ ዓይኑ የፈረጠ እና ሌሎችም ብዙ ድኩማኖች ተሰብስበው፦ በእንተ ስምዋ ለማርያም ስለቸሩ እግዚአብሔር እያሉ ሲለምኑ አይቶ ለመስጠት ሕሊናው ገፋፋውና ኪሱን ሲዳብስ አቶ ስስት በድንገት ከተፍ አለና ተው ለምን ትሰጣለህ? የወንጌል ምርኮኛ ሆነህ ተቸግረህ እንደምትሰጠው ደሀ በሰው እጅ ወድቀህ ትቀራለህ ሲለው ሕሊናው ሲያመነታ አቶ ቸርነት በቀኝ ጎኑ ጠጋ አለና ስጥ እባክህ የግዚአብሔር መንግስት የምትገኘው በመስጠት ነው እንጂ በመሰሰት አይደለም ይለዋል፡

እሱም በኪሱ የነበረችውን ሳንቲም ለድሃው ሰጥቶ ቤተ ክርስቲያን ተሳልሞ ሲአስቀድስ ቆየ። ቅዳሴውም ሲያልቅ አንድ የወንጌል መልእክተኛ የሆኑ ባህታዊ እጃቸውን አጨብጭበው ሕዝቡ ሲሰበሰብ ጸሎት አድርሰው ሰበካቸውን ጀመሩ፤ የስብከቱም ቃል እግዚአብሔር የሰው ልጅ ፈጥሮ ወደዚህ ዓለም ሲያመጣው ወጥተህ ወርደህ ሰርተህ ደክመህ በላብህ ወዝ ብላ፤ ዘፍጥረት ምዕራፍ ፫ ቁጥር ፲፯ እስከ ፲፱ ። ለተራብ አብላ ለተጠማ አጠጣ የታረዘ አልብስ የታመመና የታሰረ ጠይቅ ማቴዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፭ ቁጥር ፴፩ እስከ ፵፮ ሰው በዚህ ዓለም ቢገዛ ቢነዳ ነፍሱን ካጣ ምን ይጠቅመዋል? ማርቆስ ወንጌል ምዕራፍ ፰ ቁጥር ፴፮ ።ይላልና ያላችሁ ለሌላቸው ድኩማኖች አብሉ አጠጡ አልብሱ በሞት ስትለዩ ከአላችሁ ገንዘብ የሚከተላችሁ አንድም የለምና እያሉ ሲያስተምሩ የተሰበሰበው ሰው በነገሩ ተጸጽቶ ገሚሱ ከንፈሩን ሲመጥ ለላውም ሲያዝን አይቶ የሥጋ ምኞት በሕሊናው እያወጣ እያወረደ ወደበቱ ተመለሰ፡ መጻሕፍቶችን ሲያነብ ከቤተ ክርስቲያን የተነገርውን የስብከት ወንጌል ቃል አገኘ።

*ትንሽ ቀን እንደቆዩ በአገር ቤት ያሉ ከብቶች በድንገት የከብት በሽታ ገብቶ ሁሉንም ፈጃቸው የሚል መርዶ ደረሰው፣ ውሎ አድሮ በታላቁ ከተማ ላይ የሚገኘው የንግድ ሱቅህ በድንገት እሳት ተያይዞ ተቃጠለብህ የሚል ቃል ደረሰው፣ ውሎ አድሮ የሚወደው አሽከሩ ሞተበት፣ ጥቂት እንደቆየ በሥሬ ተተክቶ ስሜን ያስጠራዋል የሚለው ልጁ ሞተበት፣ ወደዚያው የብር አበሮቹ የነበሩት ንፍገት፣ ቅናዖት፣ ተንኮል፣ ምቀኝነት፣ ኩራት፣ ስስት፣ ሴሰኝነት፣ ቁጣና ሥጋ ምኞት ለልቅሶው እየደረሱ እግዚአብሔር ያጥናህ እያሉ ከሥጋ ምኞትና ሴሰኝነት በቀር ሌሎቹ ሁለተኛ ሳይመለሱ በዚያው ቀሩ።*

*አሁን በመከራው ጊዜ አቶ የሥጋ ምኞት መዋዕለ ዘመኑን ለሥጋው ድሎት ሲወጣ ሲወረድ ይፈጽመው የነበረውን ታላቅ ኀጢአት እያሰበ ይጸጸት ጀመር፡ እንዲሁ ሲጸጸት የክርክሩ ቀን ደረሰ።*

*የቀጠሮው ዕለት ሁለቱም ወገኖች ከአቶ መቆየት ችሎት ቀርበው ሲከራከሩ አቶ መቆየት የሥጋ ምኞትን እንዲህ ሲል ጠየቀው፡-*

*“አሁን አንተ እዚአብሔር በሰጠው ሕግ መሠረት በንስሓ ተመልሰህ ካለህ ገንዘብ ከአሥር አንድ አውጥተህ በዚህ ዓለም የሥጋህን ስም ደግነትን፣ ቸርነትን፣ ትእግስትን፣ አስተዋይነትን የሚባል ቅጽል ስም አሰጥቶህ በወዲያኛው ዓለም የእናት አባትክን ልጅ ነፍስህን በገነት ቀጠሮ ቆይታ መንግስተ ሰማያት በምትባለው የታላቅ ክብርና ንጉስ ከተማ አብራችሁ በደስታ ብትኖሩ አይሻልም?” ሲለው ያ የከብቱ፣ የአሽከሩ፣ የሚወደው ልጁ ሞት በፊቱ ድቅን ሲልበት “ኧረ እሺ ጌታዬ፤ እኔ የአቶ እንደጊዘውን ፍርድ ተከትዬ የዘለዓለም ፍርድ ተፈርዶብኝ በገሃነም ከምሰቃይ ከዚሁ ከመሬት እንዳለሁ ንስሐዬን ተቀብዬ መጽሐፉ እንደሚለው ፈጽሜ እሄዳለሁ።” ብሎ መለሰ*

***አቶ መቆየት የሚባለው ዳኛ በዚች በጸጸት ከተማ ችሎቱ የሥራ ኃደኞቹን ይዞአል፣ አቶ መንፈሳዊ ምኞት እና አቶ ሥጋዊ ምኞት ቀርበዋል።***

***አቶ መቆየት ከዚህ የሚከተለውን ፍርድ ይሰጣል፡-***

"አቶ አስተዋይ ልቦና እና አቶ እንደጊዜው የፈርዱትን ፍርድና በሁለቱም ወገን የቀረበልንን ማመልከቻ ተመልክተናል።

አቶ የሥጋ ምኞት፤ የአዳም ልጆች ጠላት የሆነው ዲያብሎስ ወገኑና ጭፍራው ሊያደርግህ የዚህን ዓለም ገንዘብን፣ ቅናትን፣ ኩራትን፣ ስስትን፣ ምቀኝነትን፣ መሬታዊ መልከ መልካም ነገሮችን በማሳየት የአዳምን ልጆች እንደ ወፍ ጫጩት ጨብጨ እይዛቸዋለሁ፣ ከቀናችው ከሕገ እግዚአብሔር አርቃችዋለሁ፣ ከእነም ጋር ወደገሀነም እንዲሀዱ ምክንያት እሆናቸዋለሁ ብሎ በመጽሐፈ መቃብያን ሣልስ ምዕራፍ ፩ እስከ ምዕራፍ ፱ የፎከረውን ተከትለህ ገሀነም ልትገባ ነበር። ዳሩ ግን ለቸርነቱ ወሰን የሌለው አምላክ ለአዳምና ለኢዮብ ለነዳዊትና ለቀሩትም ወዳጆቹ ሁሉ ያደረገላቸውን ትሩፋት ለአንተም ልቦናህን መልሶ የሰራኸውን ኀጢአት አስበህ እንድትጸጸት አድርጎ በንስሐ ገዳም ስለተገኘህ ከኀጢአት ወደ ስርየት ከክፋት ወደ በጎነት ተመልሰህ የዚህን ዓለም ተድላ ደስታ ጠፊ መሆኑን አስበህ የዚያኛውን ዓለም ደስታ ምንጊዜም የማያልፍ መሆኑን ተገንዝበህ በእግዚአብሔር ትእዛዝ እሀዳለሁ ብለህ ስለተመለስክ፣ በል እግዚአብሔር ከፈቀደልህ የመከራ ስቃይ ጊዘ ድረስ ህጉን አክብረህና ጠብቀህ ኑር። ከዕድሜህ ወዲያ መድኀኒተ ነፍስን ተከትለህ መንግስተ ሰማያትን ያውርስህ። ስል ከሥራ ቻደኞቼ ጋር ሆኜ በዛሬው ቀን የመጨረሻ ፍርዴን ፈርጃለሁ።"